

# Amhara Association in The Netherlands

## PRESS RELEASE
## ጋዜጣዊ መግለጫ
**JUNE-JULY 2026**

# ✊ የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ  የተሳካ የትውውቅ፣ የልምድ ልውውጥ እና የመታሰቢያ ፕሮግራም አከናወነ !

“አምስተርዳም፣ ኔዘርላንድ (ጁላይ 4, 2026):- የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ ጁላይ 4 ቀን 2026 በአምስተርዳም ከተማ የተሳካ የአባላትና የደጋፊዎች የትውውቅ እንዲሁም የልምድ ልውውጥ ፕሮግራም አከናውኗል። በዚህ ዝግጅት ላይ ከ60 በላይ የሚሆኑ የማህበሩ አባላት እና ደጋፊዎች የተገኙ ሲሆን፣ አዳዲስ አባላት ማህበሩን መቀላቀላቸው በደማቅ ሁኔታ ተበስሯል።

ይህ መርሐ-ግብር የትውውቅ መድረክ ከመሆን ባለፈ፣ ባለፉት የጁን እና የጁላይ ወራት በአማራ ብሔር ተወላጅና የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በሆኑት የአርሲ ነዋሪ ወገኖቻችን ላይ የደረሰውን ዘር እና እምነት ተኮር ጥቃትና ጭፍጨፋ ለማሰብ ጭምር የተዘጋጀ የመታሰቢያ ፕሮግራም ነበር።

በምሳ ሰዓት በተጀመረው በዚህ ዝግጅት ላይ፣ በመጀመሪያ የማህበሩን አመታዊ የስራ እንቅስቃሴዎች እና እቅዶች ለአዳዲስ አባላት የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል። በመቀጠልም አባላትን እርስ በእርስ የሚያስተዋውቁ የተለያዩ መሰናዶዎች በባህላዊ እንጉርጉሮ ታጅበው የቀረቡ ሲሆን፤ ከማህበሩ አንጋፋ አመራሮችም ትምህርት አዘል ማሳሰቢያዎች እና ልምዶች ተካፍለዋል።

በተጨማሪም ሃገር ቤት በጦርነት ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን የገቢ ማሰባሰቢያ የሚውል የሎተሪ እጣ ተዘጋጅቶ ነበር። ይህም በአዝናኝ መልኩ ተከናውኖ ለባለ እድለኛ አባላቶቻችን ሽልማት በመስጠት የገቢ ማሰባሰቡ ስራ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

በመጨረሻም፣ ፕሮግራሙ በግፍ ህይወታቸውን ላጡ የአርሲ ወገኖቻችን የአንድ ደቂቃ የህሊና ጸሎት በማድረግ በሰላም ተጠናቋል።










# ✊ በምስራቅ አርሲ በንጹሃን ላይ የተፈጸመውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና የኢሰመጉን 158ኛ ልዩ ሪፖርት አስመልክቶ ከአማራ ማህበር በኔዘርላንድ የ የተሰጠ የሀዘን መግለጫ !

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ባወጣው 158ኛ ልዩ ሪፖርት፤ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ አርሲ ዞን ዘጠኝ ወረዳዎች ከ2014 እስከ 2018 ዓ.ም. በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ጥቃት ይፋ አድርጓል።




በሪፖርቱ መሰረት ህጻናትና አረጋውያንን ጨምሮ ከ450 በላይ ንጹሃን በግፍ ተገድለዋል። ከዚህም በተጨማሪ በመቶዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ታፍነው ከፍተኛ ገንዘብ ሲጠየቅባቸው፣ ከ14,000 በላይ ወገኖች ደግሞ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። በርካታ አብያተ ክርስቲያናት መዘረፋቸውና መቃጠላቸውም ተዘርዝሯል። ይህ በዜጎች ላይ በስፋትና በስልታዊ መንገድ የተፈጸመው ጥቃት በአለም አቀፍ ህግ መሰረት በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀልን (Crimes Against Humanity) ሊያሟላ እንደሚችል ኢሰመጉ አመልክቷል። በመሆኑም የፌዴራልና የክልሉ መንግስታት ወንጀለኞቹን በአስቸኳይ ለፍትህ እንዲያቀርቡ፣ ለተፈናቀሉት አስቸኳይ ሰብዓዊ እርዳታ እንዲያደርጉና ተገቢውን የስነ-ልቦና ድጋፍ እንዲሰጡ ጥሪ ቀርቧል።



የአማራ ማህበር በኔዘርላንድ በዚህ ዘርና እምነት ተኮር እልቂት ክፉኛ ማዘኑን እየገለጸ፤ ለሟች ቤተሰቦች መጽናናትን፣ ለተጎዱትም ፈጣን ማገገምን ከልብ ይመኛል። ማህበሩ ፍትህና ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ የሚመለከታቸው አካላት ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ አጥብቆ ይጠይቃል። ይህ ማህበረሰባችንን ያሳዘነ ሪፖርት በአለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።




# ✊ ልዑል አስፋወሰን አሰራተ በአውሮፓ ፓርላማ በኢትዮጵያ ስላለው ቀውስ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እርምጃ እንዲወስድ ጥሪ አቀረቡ!

ኢትዮጵያዊው ምሁር፣ ደራሲ እና የንጉሣዊ ቤተሰብ ተወላጅ ልዑል አስፋወሰን አሰራተ ካሳ በአውሮፓ ፓርላማ ባደረጉት ታሪካዊ ንግግር፣ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ በኢትዮጵያ እየተባባሰ ባለው ሰብአዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ ላይ ያለውን ዝምታ እንዲሰብር አሳሰቡ። በተለይም በአማራ ህዝብ እና በኦርቶዶክስ ክርስቲያን ማህበረሰብ ላይ የተደቀነውን ጥልቅ አደጋ በማጉላት፣ የሀገሪቱን ህልውና የሚፈታተን ባለብዙ-ዘርፍ ቀውስ መኖሩን አስገንዝበዋል።



ልዑል አስፋወሰን የኢትዮጵያን የብሄር ፌዴራሊዝም ከአፓርታይድ ጋር በማነጻጸር ነቅፈው፣ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚያሳዩ አሳሳቢ መረጃዎችን አቅርበዋል። በመንግስት ሃይሎች የተፈጸሙ የድሮን ጥቃቶች እልቂትን፣ የጅምላ እስራቶችን፣ ጾታዊ ጥቃቶችን እና የትምህርት ተቋማት ውድመትን በዝርዝር አስረድተዋል። በተጨማሪም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ እየደረሰ ያለውን የተቀናጀ ጥቃት እና ሰላማዊ ድምጾችን ለማፈን የሚደረገውን ዘመቻ (ታዋቂውን አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁንን/ቴዲ አፍሮን ጨምሮ) በጽኑ አውግዘዋል።

ያለፉትን የሩዋንዳ እና የስሬብሬኒካ የታሪክ አሳዛኝ ክስተቶችን በማስታወስ፣ ልዑሉ አስቸኳይ ፍትህ እና ተጠያቂነት እንዲኖር ጠይቀዋል። የተባበሩት መንግስታት ገለልተኛ ምርመራ እንዲያደርግ፣ የአውሮፓ ህብረት የተነጣጠረ ማዕቀብ እንዲጥል፣ እንዲሁም አሜሪካ፣ የአፍሪካ ህብረት እና ዓለም አቀፍ የፍትህ አካላት ጊዜው ሳይረፍድ አስቸኳይ እርምጃ እንዲወስዱ እና ተጠያቂነትን እንዲያሰፍኑ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።




**Amhara Association in The Netherlands**

**PRESS RELEASE**
**ጋዜጣዊ መግለጫ**
**JUNE-JULY 2026**

# ✊ በአማራ ክልል በሚገኝ ገዳም ላይ በተፈጸመ የድሮን ጥቃት የሁለት መነኮሳይት ሕይወት አለፈ!

በአማራ ክልል፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ ቦረና ወረዳ በሚገኘው አባይ ገዳመ አስቄጤስ አቡነ አረጋዊ እና ቅድስት አርሴማ አንድነት ገዳም ላይ ጁላይ 22 ቀን 2026 በተፈጸመ አሳዛኝ የድሮን ጥቃት የሁለት መነኮሳይት ሕይወት ሲያልፍ፣ በ11 ሌሎች እናቶች ላይ ደግሞ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሷል። በአጠቃላይ በ14 ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱ ተረጋግጧል።

የገዳሙ አበምኔት አባ ኤልያስ ተሻገር እና የዓይን እማኝ የሆኑት እማሆይ ወለተ ማርያም እንዳረጋገጡት፣ አደጋው የደረሰው መነኮሳይቱ በአንድነት ሆነው የክረምት እህል ዝግጅት በማካሄድ ላይ በነበሩበት ወቅት በሴቶች መነኮሳይት የሥራ ቦታ ላይ ነው። ከክቡሩ የሰው ሕይወት መጥፋት በተጨማሪ፣ የገዳሙ ተግባር ቤት እና ለዓመታዊ ፍጆታ የተከማቸ እህል ሙሉ በሙሉ የወደመ ሲሆን፣ ገዳሙን የሚያገለግሉ የውኃ ማስተላለፊያ ቱቦዎችና ታንከሮችም ክፉኛ ተጎድተዋል።

በአካባቢው የድሮን አሰሳ ሲደረግ እንደነበር የገለጹት የገዳሙ አባቶች፣ ጥቃቱ ከገዳሙ ውጭ በቅርብ ርቀት ኬላ አላቸው የተባሉ ታጣቂዎችን ኢላማ ያደረገ ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውን አስቀምጠዋል፤ ነገር ግን ጥቃቱ ያረፈው ምንም በማያውቁ ሰላማዊ መነኮሳይት ላይ ነው። አደጋውን ተከትሎ የወረዳው ቤተ ክህነት ኃላፊ እና የወረዳው አስተዳደር ባደረጉት የትራንስፖርት ትብብር፣ ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው መነኮሳይት ወደ መካነ ሰላም እና ደሴ ሪፈራል ሆስፒታሎች ተወስደው የህክምና እርዳታ እየተደረገላቸው ይገኛል።



ይህ ዜና መነሻውን ከዶይቼ ቬለ (DW) አማርኛ ክፍል ያደረገ ሲሆን፣ በኔዘርላንድስ የሚገኘው የአማራ ማህበር በገዳሙ ላይ በደረሰው አሳዛኝ ክስተት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን እየገለጸ፣ ለሟች ቤተሰቦች መጽናናትን እንዲሁም ለቆሰሉት እና ለቤተሰቦቻቸው ፈጣን ማገገምን ይመኛል።






**Amhara Association in The Netherlands**

**PRESS RELEASE**
ጋዜጣዊ መግለጫ
**JUNE-JULY 2026**

# ✊ በአማራነታቸው፣ በጋዜጠኝነታቸው እና በማህበረሰብ አንቂነታቸው ምክንያት ያለ ፍርድ በእስር ቤቶች እየማቀቁ ያሉ ወገኖቻችን በአስቸኳይ እንዲፈቱ የቀረበ ጥሪ!

በአማራ ክልል ከተከሰተው የፖለቲካ እና የጸጥታ አለመረጋጋት ጋር በተያያዘ፣ በርካታ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች፣ እና የማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎች ከሦስት ዓመታት በላይ ያለ ምንም የፍርድ ቤት ውሳኔ በእስር ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻነት በመግለጻቸው እና ህዝብን በማገልገላቸው ብቻ ለእስር የተዳረጉ ናቸው። መንግስት በቅርቡ ይቅርታ ጠይቀው እንዲፈቱ ያቀረበላቸውን የጥፋተኝነት ማመኛ እና የቅድመ ሁኔታ ሰነድ፣ በርካታ ተከሳሾች «ያላጠፋነውን እና ያላደረግነውን ድርጊት ወንጀለኛ ነን ብለን አንፈርምም» በማለት በጽኑ አቋማቸው ውድቅ አድርገውታል።

እነዚህ ታዋቂ ግለሰቦች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ናቸው። በመካከላቸው ወጣቶች፣ በእድሜ የገፉ አረጋውያን፣ እንዲሁም ከመታሰራቸው ጥቂት ጊዜ በፊት አዲስ ወላጅ የሆኑ እናቶች ጭምር ይገኙበታል። እነዚህ ዜጎች ያለ ፍትህ፣ ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ለዓመታት በእስር ቤቶች እንዲንገላቱ መደረጉ፣ መንግስት በአማራ ክልል በሚገኙ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሰዎች ላይ የሚያካሂደውን ስልታዊ ጭቆና በግልጽ የሚያሳይ ነው። ተከሳሾቹ የተከሰሱበትን ወንጀል በሕግ ፊት ሳይረጋገጥባቸው፣ እና ትክክለኛ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሳይሰጥባቸው፣ በይቅርታ ስም ጥፋተኝነታቸውን እንዲያምኑ መጠየቃቸው በሀገሪቱ ሕግም ሆነ በሞራል ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም። ይህ ግልጽ የሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰት ከመሆኑም ባሻገር የፍትህ ስርዓቱን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው።



በመሆኑም፣ መንግስት የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች በማክበር፣ እነዚህን የሕዝብ ድምጽ የሆኑ ወገኖች፣ ጋዜጠኞች እና ፖለቲከኞች ላይ ያቀረበውን የሽብር ክስ ሙሉ በሙሉ በማቋረጥ፣ ፍትህን የማግኘት መብታቸው ተነፍጎ ያለ አግባብ በእስር ላይ የሚገኙትን ሰላማዊ ግለሰቦች በአስቸኳይ እና ያለ ምንም የቅድመ ሁኔታ ከእስር እንዲፈታ ጥሪያችንን በድጋሚ እናቀርባለን። ዘግይቶ የሚሰጥ ፍትህ እንደተከለከለ ይቆጠራልና ዜጎች በአስቸኳይ ፍትህ ሊያገኙ ይገባል።